በስዊድን የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ የስነጽሑፍ ክፍል በዛሬው አምዱ

## ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ!

በሚል እርዕስ ያጠናቀረውን ትንተና ያቀርባል

ሰኔ 11 ቀን 2015 ዓም (18-06-2023)

ይህ "ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ" የሚለው ግብረ ቃል በአገራችን ሕዝብ የተለመደ አገላለጽ ነው።ቃሉ በእብሪተኞች የመደፈርን ድርጊት የሚያሳይ ሲሆን በግለሰብም ሆነ በማህበረሰብ ላይ ከዚያም አልፎ በአገር ላይ የሚቃጣን ድፍረታዊ እርምጃ የሚገልጽ አባባል ብቻም ሳይሆን የተደፈረው ወገን በቁጭት በልበ ሙሉነት እንዲመክት የሚቀሰቅስ መልእክት ያዘለ ቃል ነው። የአገራችን ቋንቋ አንዱና ዋና የሆነው አማርኛ ከቋንቋው ለዛ ፣ከስነጽሑፍ ፊደላት ባለቤትነትና ጥራት ጋር ተያይዞ ሰው ሃሳቡን የሚገልጽባቸው የተለያዩ መንገዶች ስልቶችና ጥበባት አሉት፤ ከነዛም በተረትና ምሳሌ፣ግጥምና ቅኔ፣ፉከራ ቀረርቶና ሙሾ---ወዘተ የመሳሰሉት በቀጥታና በስውር ከሚጠቀምባቸው የሃሳብና የስሜት መግለጫዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በደስታና በሃዘን፣በመደገፍና በመቃወም፣በማፍቀርና በመጥላት የሚያድርበትን ስሜትና ፍላጎቱን የሚገልጽባቸው መንገዶች አያሌ ናቸው፤ከነዚያም መካከል ይህ በርዕሱ ላይ ያስቀመጥነው ምሳሌ ብቸኛ ሳይሆን በቋንቋው ውስጥ ካሉት በብዙ ሽህ ከሚቆጠሩት መካከል አንዱ ነው። ከዚህ ምሳሌ ጋር የሚመሳሰል ሌላውን ብንጨምር "ከስቴ(ቀጥኜ) ቢያዩኝ ጅማት ለመኑኝ" የሚለውም አባባል እብሪተኞች ደሃና አቅመቢስ መስሎ በገመቱት ግለሰብ ወይም ማህበረሰብ ላይ የሚሰነዝሩትን የንቀት አስተያዬትን ተከትሎ ሊመጣ የሚችለውን አደጋ በመገንዘብ ምንም ቢኮን ለግብዞች ተገዥ ሆኖ ላለማደር በአካል የማይለካና የማይገመት የስነልቦና ባለቤት መሆንን ተከትሎ ሊመጣ የሚችለውን እምቢባይነት ቁጣና እርምጃ የሚያሳይ አባባል ነው።በሰሞኑ በአጠቃላይ በሕዝቡ በተለይም በአማራው ማህበረሰብ ያዬነውና የተገነዘብነው ስሜት እነዚህን ምሳሌዎች የሚያንጸባርቅ ሆኖ አገኘተነዋል።

ለዓመታት ሰብአዊ ክብሩን በማሰብና የፈጣሪን ሕግ በማክበር ለሰላም ቅድሚያ በመስጠት በትእግስትና ይቅርባይነት አንድነቱን ጠብቆ የኖረው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለይም የአማራው ተወላጅ ይህንን ገጸባህሪውን በሚጠሉና በሚቀናቀኑ፣የትንሽነት ስሜት ባሳበዳቸው፣በኋላ ቀር አስተሳሰብ ውስጥ በሚዳክሩ፣ለውጭ ወራሪዎች በባርነት መገዛትን እንደ ትልቅ ጸጋ በሚቆጥሩ ድኩማን የፍርሃት ትርጉም ተሰጥቶት የሚያደርሱበትን በደልና ግፍ በመጨመር አሁን ካለበት ደረጃ ላይ አድርሰውታል። ለእኩልነትና ለፍትሕ ብሎም ለሰብአዊ ፍጡር ያለውን አክብሮት በፈሪነትና በአጎንባሽነት ተርጉመው ጭራሽ ለማስጎንበስ ያልፈጸሙበት ግፍና በደል የለም።የጋራ የሆነች አገር መመስረቱና ለተከታዩ ትውልድ ማስረከቡን እንደሃጢያትና ወንጀል ቆጥረው የእኛ ጎሳ የሚሉት ትውልድ የአውሬነት ስሜት አድሮበት አብሮት በኖረው ብቻም ሳይሆን በትውልድ እትብት በተሳሰረው ወገኑ ላይ ተነስቶ በጠላትነት እንዲያዬውና እንዲጨፈጭፈው አድርገውታል።እራሱን ከሌላው መሰል ወገኑ ነጥሎ፤ይዞት የኖረውን የጋራ ባህሉን፣እምነቱን፣ፊደሉንና ቋንቋውን እርግፍ አድርጎ ጥሎ የባዕዳንን ባህል፣እምነት፣ ፊደል ተሸክሞ ማንነቱን እንዲከዳ ፣ባርነትን ወዶ እንዲቀበል፣ነጻነቱንና የትልቅ አገር ባለቤትነቱን ተገፎ በጠባብ መሬት ውስጥ የሚተራመስ አገልጋይ እንዲሆን ፊደል ቆጥረናል የሚሉ የራሱ ጎሳ ተወላጅ የሆኑ ባንዳዎች ፈርደውበታል።

በየጊዜው በተለይም ላለፉት ግማሽ ዘመን ሲሆነው በተጠጋው ጊዜ በስልጣን ላይ የወጡት አምባገነኖች ለአገዛዛቸው ያልተመቸውን ማህበረሰብ ፣ዜጋ በማጥፋት አገራችን ላለችበት ምስቅልቅል ሁኔታ የበኩላቸውን ድርሻ አድርገዋል፤እያደረጉም ነው።ሰላምና ዴሞክራሲ በሰፈነባቸው አገሮች 50 ዓመት ቀርቶ 5 ዓመት የእድገት ለውጥ የሚታይበት ጊዜ ነው።50 ዓመትማ የሌሉ አገሮች ተፈጥረው ለዘመናት የቆዩትን አገሮች መቅደም ብቻም ሳይሆን እንደ ኢትዮጵያ ዘመናት ላስቆጠሩት አገሮች የእርዳታ እጃቸውን የሚዘረጉ ሃብታምና ሰላማዊ አገር ለመሆን ችለዋል።በጣም የሚያስገርመው እነዚህ አገሮች ከኢትዮጵያ የተሻለ የአዬር ጠባይ፣ለም መሬትና ብዙ ሕዝብ ኖሯቸው ሳይሆን ሙሉ ለሙሉ በርሃማ አዬርና የአሸዋ ክምር የሸፈናቸው መሆናቸው ነው።ያላቸው የኤኮኖሚ መሠረታቸው ብዙም ሳይሆን በዋናነት የነዳጅ ክምችት በመያዛቸውና ያንንም ለመጠቀም በመቻላቸው ነው።በሚያገኙት ገቢ የውቅያኖስ ውሃ በመጥለፍ በርሃውን ለእርሻ ና ለኑሮ የተመቸ አድርገውታል፤ ለነዋሪው ሕዝብም የመጠጥ ውሃ እቤቱ ድረስ ቧምቧ ዘርግተው ያደርሱለታል።በአጭሩ ገሃነሙን ወደ ገነት ለውጠውታል ማለቱ ይቀላል።

ሕዝባቸው ጠግቦ ማደር ብቻም ሳይሆን የዘመኑን ከፍተኛ የኑሮ ደረጃ እንዲኖር አድርገውታል፤ ሌብነትና ሙስናን ሙሉ ለሙሉ ባያጠፉትም፣የጥቂቶች ፈላጭ ቆራጭነት ቢኖርም ሕዝቡ መደበኛ ፍላጎቱ እንዲሟላም ብቻ ሳይሆን የወደፊቱ ፍላጎቱን ሊያሟላ በሚችልበት ደረጃ አዘጋጅተውታል። ያም ለነዋሪው ሰላምና እርካታን ሰጥቷል።ለብዙ አገሮች ዜጎች ሥርተው ለመኖር የሚችሉበትን ዕድል ከፍቶላቸዋል።በሥልጣን ላይ ያሉት መሪዎችና ስርዓታቸው ምንም እንኳን የዴሞክራሲ ውጤቶች ባይሆኑም አገር ወዳዶች ናቸው።እዬበሉ ሕዝቡን በርሃብ የሚቀጡ ሳይሆኑ ምንም እንኳን የጉርሻቸው መጠንና አይነት ቢለያይም በልተው ያበላሉ።እነሱ ሲያፍሱና ሲዝቁ ለቀረው ዜጋ በእፍኝም ቢሆን ያካፍሉታል።የሕዝቡ በትምህርት አለመግፋትና በሃይማኖት ሰበብ መተብተቡ ለጊዜውም ቢሆን ዕድል ቢሰጣቸውም ቀስ በቀስ የትውልዱ አስተሳሰብ እዬተቀዬረ በመምጣቱ የአክራሪነት አቋም በዘብተኛነት በመተካት ላይ ነው።በተለይም በሴቶች መብት ዙሪያ ያልነበሩ ልማዶች በመለመድ ላይ ናቸው። የወደፊቱ መዳረሻ ባይታወቅም የሚሻል እንጂ የማይሻል እንደማይሆን ከትውልዱ አስተሳሰብ ለማወቅ ይቻላል።

በሌላ በኩል ደግሞ ገነት የነበረውን አገር ወደ ገሃነም ለውጠው ሕዝባቸውን የስቃይና የመከራ ኑሮ ገፈ ያደረጉም ብዙ ናቸው ፤ከነዚያ ውስጥ በዓለም የሚታወቀው በኢትዮጵያ ውስጥ የሰፈነው ስርዓት ነው። የሚታዬውና የሚሰማው ሁሉ መንግሥት አለ በሚባልበት አገር ውስጥ የሚሆን አይደለም። እንኳንስ መንግሥት ቀርቶ ትንሽ የሰውነት ጸባይ ያለው ሽፍታ የሚቆጣጠረው መንደር አይመስልም። ኢትዮጵያ ከሰማይ የወረደ መቅሰፍት የሚቆጣጠራት አገር መስላለች።

የሰው ልጅ እንደ ዶሮ የሚታረድባት፣አራጁ በነጻነት በፈለገው ቦታ ሲሸከረከር ዜጋ በተወለደበትና በኖረበት መሬት ለመኖር ቀርቶ ሞቶ የማይቀበርባት፣ገዳይ ያሻውን አድርጎ ተሸልሞ የሚቀመጥበት፣ የጭካኔ ከፍታ የሚታይባት ምድር ሆናለች።በወረራ ብዙ ሕዝብ የጨፈጨፉ ወንጀለኞች እንደ ብሔራዊ ጀግና ተቆጥረው የክብር አቀባበል የሚደረግላቸው ፣የሰላምና የፍትሕ ተቆርቋሪ ተብለው የሚወደሱባት ፣ሁሉም ነገር በግልብጡ የሚታይባት አገር ሆናለች።እርሃብ ሰፍኖ የጥጋብ ፣ድርቅ ሆኖ የምርት ብዛት፣ጦርነትና ጭፍጨፋ ሲካሄድ ሰላም የሰፈነባት፣የመበታተን አደጋ ሲያንዣብብ አንድነቷ የተረጋገጠባት ፣በጎሳ ማንነት ጭፍጨፋ ሲፋፋም፣መግባባትና እኩልነት የሰፈነባት እዬተባለ ሁሉም ነገር የተገላቢጦሽ የሚተረጎምባት አገር ሆናለች።

የዚህ ሁሉ የውሸት፣የጭካኔ፣የክህደት፣የዘረፋና ሌብነት፣አገር የማፍረስ ፊታውራሪ ላለፉት 32 ዓመታት ሥልጣኑን በጉልበት እዬተቀያዬረ የተቆጣጠረው ጸረ ኢትዮጵያ የሆነው የወያኔና የኦነግ ጥምር ሃይል

ነው።ወያኔ ከሰሜን ፣ ኦነግ ከምዕራብ ፣ከመሃልና ምስራቅ በኩል ጦር እዩሰበቁ ላለፉት 32 ዓመታት የአገራችንን አንድነት ሲፈታተኑ ኖረዋል።ኢትዮጵያን የሰው ልጅ የሚታረድባት ቄራ አድርገዋታል። ለአለፉት 5 ዓመታት የሥልጣን ቦታ በመቀያዬር ኦነግ የበላይነቱን ይዞ ከሁሉም ጊዜ የበለጠ አገር የማፍረስ ዘመቻውን ተያይዞታል።ለአገሪቱ ዋልታና ማገር በሆኑት ቤተ እምነቶችና ማህበረሰቦች ላይ የከተት አዋጁን አውጆ ብዙ የሃይማኖት አባቶችና ምእመናን ተጨፍጭፈዋል።በዚህ ጸረ እምነት ዘመቻ ቤተክርስቲያን፣ገዳማትና መስጊዶች ወድመዋል።ንብረቶች ተዘርፈዋል።የኦርቶዶክስ ተዋህዶና የእስልምና እምነት ተከታዮች ለስርዓቱ ኢትዮጵያን የማፈራረስ ዓላማ እንቅፋት ናቸው ተብለው በመመደብ እንዲጠፉ ተፈርዶባቸዋል።በመጀመሪያ በስርዓቱ ታዛዦች ቁጥጥር ስር እንዲውሉ በማድረግ አማኙን በጎሳና በክልል ከፋፍለው እርስ በርሱ እንዲባላ በማድረግ ጥፋቱን በአገር ወዳዱ ምእመናን ላይ ደፍድፈው ማሳደዱን ሙያቸው አድርገውታል። የራሳቸውን ታዛዥ ግለሰብ እዩመረጡ በመሾም ቤተእምነቶችን ሲደፍሩ ፣በሚጨፈጨፈው ሕዝብ መኖሪያ መሬት ላይ ወንጀለኞች በነጻነት ሲምነሸነሹ ታዝበናል።ይህ ሁሉ ድፍረት ከእብሪትና ንቀት የመነጨ በመሆኑ  ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ የሚለውን ምሳሌ ለጽሑፋችን እርዕስ አድርገነዋል።

ለአገሩ ትልቅ ፍቅር ያለውን ማህበረሰብ የሚኖርበትን ቦታና ቤት እዩነጠቁና እያፈረሱ ሜዳ ላይ የማፍሰሱ ተግባርም የዚያው አገር የማፍረስ አካል ነው።ዜጋ ሕገወጥ ነዋሪ እዩተባለ እንደ አውሬ እዩታደነ ሲባረር፣ሲገደል እያዩ መቀመጥ ለሕሊና ይከብዳል።ሕጻናትና አዛውንቶች ባልፈጸሙት ወንጀል፣ኢትዮጵያዊ በመሆናቸውና በጎሳ ማንነታቸው ፍርድ አልባ ጥቃት ሲደርስባቸው እያዩ መቀመጥ በራሱ የወንጀሉ ተባባሪ መሆን ነው።ይህንን ግፍና መከራ አልቀበልም ፤በቃኝ ያለውን እያሳደዱ ሲያስሩ፣ሲረሽኑ፣በዝምታ የሚያልፍ ቢኖር ነገ በራሱ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ተመሳሳይ አደጋ በጸጋ ለመቀበል የቆረጠ ከሰው ደረጃ የወረደ እንስሳ ነው።

ጥቂቶች ለብዙ ዓመታት ሲታገሉለትና መስዋእት ሲከፍሉበት የኖረውን የሙብትና የህልውና ጥያቄ ለዓመታት በዝምታ የግፍ ጽዋ ሲጨልጥ የኖረው አገር ወዳዱ አማራ አሁን ላይ  እቤቱ ድረስ ሊጨርሱት ሲመጡ ተቀምጦ የሚጠብቅበት ሁኔታ አለመኖሩን በግልጽ እያሳዩ መጥቷል፤በሚችለው መንገድ ሃይሉን አሰባስቦ ለመኖር ወይም ላለመኖር የሚወስንበትን የህልውና ትግል ጀምሯል።በከተማ በገጠር ለአገር አንድነት፣ለእኩልነት፣ለፍትሕና ለዴሞክራሲ የሚታገለው ዜጋ ቁጥሩ ከቀን ወደ ቀን እዩጨመረ በመሄድ ላይ ነው።ይህንን የተገነዘበው የአገር አጥፊው የወያኔና የኦነግ ስብስብ አሁን ከሙቼውም ጊዜ በበለጠ ተደራጅቶ የሞት የሽረት ትግል ለማድረግ በመንቀሳቀስ ላይ ነው።ይህ የባንዳ ስብስብ ከውጭ አጋሮቹ ጋር ሆኖ የጀመረውን ጸረ ኢትዮጵያና ጸረ አማራ ትግል ሁሉም አገር ወዳድና ሰብአዊ ፍጡር ሊቃወመውና ሊታገለው ይገባል።

አገር አጥፊው ቡድን በጦር ሜዳ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት ብሔራዊ ምልክትና መታወቂያ በሆኑት ፣በባሕልና ቅርስ፣በቋንቋ፣በሰንደቅዓላማ ላይ ዘመቻ ማድረጉን ቀጥሎበታል።በኤኮኖሚውም ዘርፍ እንዲሁ ለዓመታት ተገንብተው ጥሩ ስምና ዝና ያተረፉትን ተቋማት በማፍረስ፣በመሸጥና በመለወጥ ላይ ተሰማርቷል።ከነዚያም ውስጥ ከአፍሪካ ፣የመጀመሪያና ተወዳጅ ፣በዓለም ደረጃም አሉ ከሚባሉት ውስጥ ታዋቂና ተወዳዳሪ የሆነው የኢትዮጵያ አዬር መንገድ ገበያ ላይ ከቀረቡት አንዱ ነው።ቀደም ሲል የቴሌ፣የስኳርና የሲሚንቶ ፋብሪካዎችን የቸበቸበው የዘራፊ የኦነግ ስብስብ ፊቱን ወደ አዬር መንገዱ በማዞር በመጀመሪያ የጭነት (ካርጎ) ክፍሉን ከዚያም አመንምኖ ሌላውን ለመሸጥ ያወጣውን መመሪ ለማስፈጸም ለብዙ ዓመት አዬር መንገዱን በተለያዩ ቦታዎች ያገለገሉትን ኢትዮጵያዊ አገር ወዳድ የሆኑትን አቶ ግርማ ዋቄን ከነበሩበት ሃላፊነት ላይ አንስቶ በምትካቸው ስለ ሲቪል አቪዬሽንና ስለአዬር መንገዱ አሠራር ምንም እውቀት የሌለው፣ የአዬር ሃይሉ

አዛዥ የሆነው የኦነግ አባል ጀነራል ይልማ መርዳሳ ቦታውን እንዲረከብ ተደርጓል።ምንም እንኳን አቶ ግርማ ዋቄ ለምን እንደለቀቁ ምክንያቱን በግልጽ ባያስቀምጡም በስምምነት የተሰራ አሻጥር ሊኖር መቻሉን ፣በእሳቸው አመራር በሚስጥር ለናይጀሪያ የተሸጡ አውሮፕላኖች መኖራቸውንም ስንሰማ አቶ ግርማ ዋቄ ያሻጥሩ አካል ሆነው ይሆን የሚል ጥያቄ ጭሮብናል።የአቶ ግርማ ቦታውን መልቀቅ መንደርደሪያ የሆነውም በኦነጎች እቅድ ጀነራል ይልማ መርዳሳ ለዛሬው ሹመት እንዲበቃ ከሁለት ዓመት በፊት በጃንዋሪ 2021 በኢትዮጵያ አዬር መንገድ በቦርድ አባልነት ሲመደብ ለቀጣዩ ተልእኮ ያገለግላል ተብሎ እንጂ አዬር መንገዱን ያሳድጋል ተብሎ አይደለም።አቶ ግርማ ዋቄ ያንን አለመቃወማቸው በራሱ ለምን የሚል ጥያቄ ያስነሳል።ቀጣዩ የኦነጎች እርምጃ አዬር መንገዱን አዬር በአዬር የመሸጡ ሂደት ይሆናል።በምትኩ የኦሮሚያ አዬር መንገድ ለማቋቋም በእድሳት ስም አዬርመንገዱን ከቦሌ አንስቶ ደብረዘይት ለማዛወር ብዙ ሚሊዮን ብር ተመድቦ ዝግጅቱ በመካሄድ ላይ ነው።ከሁሉም በፊት ግን የሚከተሉትን መፈጸም የኦነጎች ቀዳሚ ተግባር ነው።

1 መጀመሪያ የኢትዮጵያን ግዙፍ መታወቂያ ማሳጣትና ብሔራዊ ሃብትን መዝረፍ

2 በቀጣይም ስርዓቱ የገጠመውን የውጭ ምንዛሪ በማግኘት ያቀደውን የኦሮሚያ አገር ግንባታ እቅድ ማስፈጸም ።

ለማንኛውም ሹመት የሚያስፈልገው መለኪያ የጎሰኛው ስርዓት ተወላጅ፣ ታማኝና አገልጋይ ከዚያም በላይ ለኦነግ አገር የመበታተን ተግባር የሚሰለፍ መሆኑ የሚታመንበት መሆንን ይጠይቃል።ይልማ መርዳሳም ለአዬር ሃይሉ አዛዥነት የታጨው ከዚያ አኳያ ሲሆን ያሁኑም ሹመት የዚያው ነጸብራቅ ነው። ከሹመቱ ጋር የተያያዘው ሌላው ግዳጁ በአዬር መንገዱ ውስጥ የነበሩትን የሌላ ጎሳ ተወላጆች እያባረረ በኦሮሞ ተወላጆች በመተካት የኦሮሞ መሳይ አዬር መንገድ የማድረግ ተልእኮ ነው።ይህ ሰው የአብይ አህመድ ታዛዥና ቀኝ እጅ በመሆን በሕዝብ ላይ ድሮንና ተዋጊ አይሮፕላን አዞ በቦምብ ሲደበድብ ትንሽ የማይሰማው ጨካኝ ሰው ነው።ለፍርድ እንጂ ለሹመት መታጨት የሌለበት ወንጀለኛ ነው።

በሌላም አቅጣጫ አገራችን በነዚሁ አገር ጠሎች ምክንያት የራሷን ወደቦች አጥታ የሌሎች ጥገኛ የሆነች ቢሆንም፣ ምንም እንኳን ወደብ ሳይኖራት የባሕር ሃይልና የንግድ መርከብ መያዟ ቢያስገርምም በከባቢው ሽቀጥ በማመላለስ ላይ የተሰማሩት መርከቦቿም ቢያንስም ቢበዛም፣ቢዘረፍም የውጭ ምንዛሬ ማስገባታቸው አይካድም።በተጨማሪም የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማና ታሪካዊ የታሪክ መገለጫዎችንና ቦታዎችን ስያሜ የተሸከሙ ናቸው።ይህም ማንነታቸው ለገበያ ከቀረቡበት አንዱ ምክንያት ይሆናል ብለን እናምናለን። የተሸጡት ተሸጠው ላልተሸጡት ቀሪዎቹ ለመሸጥ ደላላ ተመድቦ ገዥ በማፈላለግ ላይ መሰማራቱ ተሰምቷል።ኦነግና ወያኔ አገር እንመሰርታለን በሚል ቅዠት የኖረች አገር ለማፈራረስና ለመቀራመት የማይገለብጡት ድንጋይ የለም።

ሌላው ግዙፍ የሥርዓቱ ክህደት ደግሞ በአባይ ግድብ ዙሪያ የተፈጸመው ብሔራዊ ክህደት ነው።የሰኔና ሃምሌ ወር የግድቡ ውሃ ሙላት የሚከናወንበት መሆኑ ሲታወቅ እንዳለፉት ጊዜያቶች ስለሙሊቱ ምንም አለመነገሩ፣የሙሊት ከፍታ ማሳያ ምልክቶች እንዲጠፉ መደረጉ ከዚህ በፊት ይነሱ የነበሩትን ጥርጣሬዎች ይበልጥ ጎልተው እንዲወጡና እንዲታመኑ አድርጓቸዋል።ለግድቡ ወጣ የተባለው ገንዘብ መጠን ሕዝብ አዋጣ ከሚባለው ጋር ሲመጣጠን በጣም ከፍተኛ ነው።፣ገንዘቡ ከዬት መጣ ?የሚል ጥያቄ ተነስቶ መልስ አለማግኘቱ ሲገርም ይመነጫል የተባለው ሃይል የት እንደደረሰ፣ሕዝቡም ከነበረበት የጨለማ ኑሮ ፈቀቅ እንዳላለ ሲታሰብ የግድቡን የኢትዮጵያዊ ሃብት መሆን ከጥርጣሬ ውስጥ ይከተዋል።በአመዛኙ ግድቡ ተሸጧል ለማለት የሚያስደፍር ደረጃ ላይ ደርሰናል።ትንሽ

የባለቤትነት ድርሻ ብትኖርም አነግ ባቀደው መሠረት ከባቢውን ተቆጣጥሮ የራሱ ለማድረግ በቤንሻንጉል ክልል  መንቀሳቀሱ ማሳያና ማረጋገጫ ነው።ምናልባትም በዚህ የጥቅም ግጭት ከወያኔዎች ጋር ግብግብ ሳይፈጠር አይቀርም።ወያኔም ቀድሞ ያቀደው ስለሆነ ጥቅሙን አሳልፎ አይሰጥም።ይህ የሚሆነው ግን የኢትዮጵያዊው አገር ወዳዱ አቅም ካጣና ከተሸነፈ ብሎም በኢትዮጵያ ፍርስራሽ ላይ ብቻ ነው።

ዘረፋና ስርቆት መገለጫው የሆነው የወያኔ/አነግ አገዛዝ  ከአገር ሃብት አልፎ በዓለም መንግሥታትና ድርጅቶች ለተቸገሩት ዜጎች የተላከውን የእርዳታ እህል፣መድሃኒትና አልባሳት እዬነጠቁ ለጎረቤት አገራት መቸብቸባቸውን ላኪዎቹ ተከታትለው ደርሰውበታል።በዓለም ታሪክ ውስጥ የእርዳታ ስጦታ ከሕዝብ ጉሮሮ ነጥቆ የሚበላ መንግሥት ያለባት አገር ኢትዮጵያ ሆናለች።

ለአገር ደንታ የሌለው ቡድን የአገር ጥቅምና አንድነትን ለማስጠበቅ እንደማይችል ይታመናል።ከዚያ ባለፈ የኔ ነው የሚለውን ጎሳ ሳይቀር እምነቱን ባህሉንና ማህበረሰብአዊ እሴቶቹን፣የተፈጥሮ ሕጎችንም ንዶ ፣ትውልድን የሚያቀጭጭና የሚያጠፋ የግብረሰዶም ልማድና ተግባር ለማስፋፋት በነጻነት ስም ደፋ ቀና ሲል ማዬቱ በተለዬ መንፈስ የሚነዳ ልዩ ፍጡር ያደርገዋል።ይህ ቡድን ጸረ ሰውና ጸረ ትውልድ ቡድን ነው።በትምህርት ሚኒስቴሩ በኩል የትምህርት ክፍለ ጊዜ ተሰጥቶት ወጣቱን ትውልድ ለመበከል መመሪያ መውጣቱ ታውቋል።ይህንን የጥፋት መንገድ ሁሉም የሃይማኖት ተቋማትና ምእመናን እንዲሁም የሰው ዘር በዓለም ላይ ተባዝቶ  የመኖር መብቱ እንዲከበርት የሚታገሉ ሊቃወሙትና  ተጠያቂውን መንግሥት ነኝ ባይ አገር አጥፊ ቡድን ከሥልጣን መንበሩ ሊያሶግዱት ይገባል።ለገንዘብና ለጥቅም ሲል የነጮቹን እርኩስ ምግባር በአገር ሕዝብ ላይ መጫን ከክህደትም ክህደት ፣ከወንጀልም በላይ ወንጀል ነው።በቦሌ መንግድና በዬምሽት ቤቱ የሚርመሰመሰው ግብረሰዶማዊ፣ምህዳሩን አስፍቶ በኪነጥበብ መድረኮች ተዋቂነትን ባተረፉ ተዋንያን (አርቲስቶች)ዙሪያ ዘንድ የዘመናዊነት መታወቂያ እዬሆነ መጥቷል።ይህ ዘመናዊነት ሳይሆን የጥፋት ውሃን ያስከተለ የዓለም መቅሰፍት ምልክት ነው።ስለሆነም ሳይስፋፋ ማሶገድ ይገባል፤ሳይቃጠል በቅጠል!ይህ ማለት በድርጊቱ የተሳተፉትን ማጥፋት ሳይሆን በድርጊቱ የተለከፉትን ከድርጊቱ የሚርቁበትን የሕክምናና የማህበረሰብአዊ ድጋፍ ማበርከት ቅድሚያ ሊሰጠው እንደሚገባ ለማሳሰብ ነው።

ሌላው የባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ ትዝብታችን የሚነሳው ይባስ ብሎ የጎሰኞቹ የብልጽግና ተብዬው ቡድን ባሕርዳርን የአድማ መምቻቸው ማእከል አድርጓት መከረሙ ነው።በአማራው ላይ ለሚወስዱት ጭፍጨፋ እቅድ የሚያወጡት በዚችው የአማራ ክልል ከተማ በሚሏት ባሕርዳር ውስጥ ነው። ብዙ አማራዎችን የጨፈጨፈው አሁንም ለመጨፍጨፍና የወልቃይትና ራያን ለም መሬት ነጥቆ ነጻ ትግራይን ለመመስረት የሚንቀሳቀሰው የወያኔ መሪ ጌታቸው ረዳ ከብአዴን ጋር የተፈራረመው በዚቹ ባሕርዳር ከተማ ነው።በሁለት ባላ ላይ የተንጠለጠለው የወያኔ ቡድን በደብረጽዮን፣ በነጻድቃንና በሌሎቹ  በኩል ጦር እዬሰበቀና ወራሪ እያዘጋጀ  ለዚያ ማዘናጊያ የሚሆን የሰላምና የእርቅ መልእክቱን በጌታቸው በኩል እዬላከለማዘናጋት ሞክሯል።በዚቹ ከተማ ለመብቱ የሚታገለው አማራ ይገደላል፣ ይታፈናል።ግድያና አፈናው የሚፈጸመው በጉልበት ጥሰው በገቡ የአነግ ወራሪ ሰራዊትና የክልሉ የብልጽግና ተብዬው ሹመኞች ትብብር ነው።በሆድ አደሮች የሚታገዘው ይህ ወረራ ግን የታሰበውን ውጤት  ሳያገኝ የብዙ አነጋውያን ወጣቶች ህይወት የሚቀጭበት ሆኗል።የወያኔ ወራሪም በራያ ና በወልቃይት በኩል ተመሳሳይ ሙከራ እያደረገ ንጹሃንን እዬገደለ ነው።እነዚህ የጥፋት ሃይሎች ሰራዊት ከባቢውን ለቆ ካልወጣ ያሞራ ሲሳይ የመሆን እጣው ከፍተኛ ነው።ምንም ጊዜ ቢሆን ሕዝብ የተሸነፈበት ጦር ሜዳ የለም።የማታ ማታ ድሉ የሕዝብ ነው።ያ የድል ቀን እንዲመጣ ሁሉም አገር ወዳድ ከአማራው ወገኑ ጋር ለትግል መሰለፍ ይኖርበታል።ሳይታገሉ ወይም ለትግሉ በሚችሉት

መንገድ ሳያበረክቱ የሚገኝ ነጻነት፣ክብርና መብት አይኖርም።ቤቱ የፈረሰበት፣ከሥራው የተባረረው፣ በርሃብ አለንጋ የሚገረፈው፣በሥራ አጥነት ኑሮ የጨለመበት፣ቤተሰቡ የታረደበት፣የተጨፈጨፉበት፣ የእምነት ተቋሞቹ የፈረሱበት፣በእምነቱና በማንነቱ ምክንያት መከራ የሚደርስበት ወጣት ሽማግሌ--- ወዘተ ሁሉ በአንድ ላይ እጅ ለእጅ ተያይዞ መነሳትና አገሩን ከጥፋት እራሱንም ከችግርና ከመከራ ፣ ከስደትና ከድህነት ነጻ የሚያወጣበት ጊዜው አሁን ነው።እምቢ ብሎ በስርዓቱ ላይ ተነስቶ የራሱን ኢትዮጵያዊ የሆነ ፍትሓዊ ስርዓት ለመመስረት ይነሳ!ማልቀስና ማላዘን፣በውጭ ሃይሎች መተማመን ይብቃ! ጠላትና ወዳጁን ለይቶ ይቁም!

በውጭ አገር የምትኖረው ኢትዮጵያዊ ሆይ

በውሃቀጠነ ልዩነት፣በጎጥ አስተሳሰብ፣ለግል ጥቅምና ክብር፣ለቡድንና ሰፈርተኝነት ህሳቤ ተነጣጥለህ የምታካሂደው ንትርክና ትግል ይበልጥ ይጎዳል ፣ለአጥፊ ሃይሎች ጥቅም ይሰጣል እንጂ ለኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጠቅም ነገር አያመጣም፤አንተንም የሚያኮራ ታሪክ ባለቤት አያደርግህም።ስለሆነም አገር አድን ትግል የሚያካሂደውን ብሔራዊ ግንባር ተቀላቀል!በምትችለው ሁሉ እዩረዳህ ሃይሉን አጠናክር!በአስረሽ ምችው ከንቱ ዝግጅት ገንዘብና ጊዜህን ጉልበትና እውቀትህን አታባክን።አገር ሲታመስ፣ሕዝብ በመከራ ውስጥ እያለ ለጭፈራና ለመዝናናት አገር አቋርጠህ አትሂድ።እዩዩም ሲደላ ነውና ያንን አገር ሰላም ሲሆን ትደርስበታለህ።የወገን ምንነቱ የሚለካው በመከራ ጊዜና አገርና ሕዝብ በፈተና ላይ በሆኑበት ወቅት ነው።በእስፖርትና የባሕል ዝግጅት ሽፋን በአውሮፓ ከተማ በአመስተርዳምና በአሜሪካ በዳላስ ከተማ በማዘጋጀት ከትግል መስከ ሊያሶጡህና ለወንጀለኛው የጎሰኞች ስርዓት የፖለቲካ ሽፋን ለመስጠት ሊጠቀሙብህ ያሰፈሰፉትን ሆድ አደሮች አሳፍራቸው። በዚህ ዝግጅት ገንዘብ እንሰበስባለን ብላችሁ የቋመጣችሁም ወደ ቀልባችሁ ተመለሱ እንላለን።ከሞኝ ደጃፍ ሞፈር ይቆረጣል እንዲሉ ብልጣ ብልጦች አታለው ሊዘርፉህ፣ከዓላማህ ሊነጥሉህ ሲመጡ አሳፍረህ መልሳቸው።አሁን ጊዜው የምትታገልበት እንጂ የምታውደለድልበት ጊዜ አይደለም።

ትንታኔያችንን ከመደምደማcne በፊት በቅርቡ በrbaHeርዳር ከተማ የተደረገው የኦነግ መራሹ የብአዴን ስብስብ በዝግ ተሰብስቦ ያሳለፈውን ውሳኔ ለማቅረብ እንወዳለን።

1- ማዳበሪያ የሚጠይቁ አርሶ አደሮችን የሚለቅምና የሚያፍን ኮሚቴ ማቋቋም
2- ሕዝቡን የሚቀሰቅሱትን እያደነ በጥቅም የሚደለሉትን በመደለል እምቢ በሉት ላይ እርምጃ የሚወስድ ቡድን ማቋቋም
3- ወጣቱን በፋኖ መልክ በማዘጋጀት ክፍፍል የሚፈጥር አካል መፍጠር
4- በሁሉም ወረዳ የሃይማኖት አባቶችና አረጋውያን ሕዝቡን እንዲያረጋጉና ከስርዓቱ ጎን እንዲሰለፉ ማድረግ
5- በከፍተኛ አመራሩ ውስጥ ለውጥ የተደረገ የሚያስመስል ሥራ መሥራት
6- የክልሉ መሥሪያቤቶች በጀት መድበው ፋኖን የሚዋጋ ሚሊሽያ እንዲያዘጋጁ ማድረግ
7- የአማራ ባለሃብቶች ለመከላከያ ጦሩ የገንዘብ እርዳታ እንዲያደርጉ ትእዛዝ ማስተላለፍ
8- በሚስጥር ፋኖን የሚረዱትን የተደረሰባቸውን 23 ሰዎች ለፖሊስ አሳልፎ መስጠት
9- በውጭ አገር ያለውን የግንኙነት መረብ የሚቆጣጠርና የሚያከሽፍ የዲጂታል ቡድን ማጠናከር

በእኛ በኩል እነዚህን የኦነግ ኦሕዴድ የጥፋት እቅዶች ለማምከን ይበልጥ ተደራጅተንና ተባብረን ትግሉን ማጠናከር ይጠበቅብናል እንላለን።

በአንድነት፣ለአንድነት እንሰለፍ!

ሕዝባዊ ግንባር ያሸንፋል!!

ኢትዮጵያ በነጻነትና በአንድነት ለዘለዓለም ትኑር!!